# የንጥር-ጥናት አውትላይኖች

## አንደኛ እና ሁለተኛ ዜና፣ ዕዝራ፣
## ነህምያ እና አስቴር

### ቁልፍ መግለጫዎች

በብሉይ ኪዳን ያሉት የአሥራ ሁለቱ የታሪክ መጻሕፍት
(ኢያሱ፣ መሣፍንት፣ ሩት፣ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት፣
1ኛ እና 2ኛ ዜና፣ ዕዝራ፣ ነህምያ እና አስቴር) ውስጠ መሠረታዊ ትርጉም
በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ለከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መገለጡ
አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለማጠናቀቅ
ቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ለማፍራት
እና ለመገንባት ሰው በሕይወት እና በባሕርይ (ተመላኪነቱን ሳይጨምር)
እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው በመሆን
ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለማከናወን መንገድን የማዘጋጀቱ መገለጥ ነው።

ዕዝራ የእስራኤልን ሕዝብ በሰማያዊ እውነቶች መልሶ አቀናበራቸው፤
በጌታ ምለሳ እግዚአብሔርን የሚገናኙ፣ በእግዚአብሔር ተሞልተው የረኩ፣
ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆኑ፣ በእግዚአብሔር የተሞሉ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የሚያውቁ—
በምለሳው ውስጥ አስተማሪ ለመሆን ብቁ የሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ሰው—
ካህን አስተማሪዎች፣ ዕዝራዎች ያስፈልጉናል።

ቤተ ክርስቲያንን እንደ የእግዚአብሔር መገለጥ መገንባት እንችል ዘንድ
በክርስቶስ መኖር እና ክርስቶስን መኖር፣ ከዚህም የተነሣ ክርስቶስን ማጉላት ያስፈልገናል፤
እግዚአብሔርን ለመግለጥ፣ ለሙሽራችን ለክርስቶስ
እንደ ንጽሕት፣ ክብርት፣ እግዚአብሔርን-የምትገልጥ ሙሽራ ሆኖ ለመቅረብ
በቃሉ ውኃ ማጠብ በየዕለቱ መቀደስ እና መታደስ ያስፈልገናል።

ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል መገንባት፣
በአራት መርሆች መሠረት የሚከናወን
የመንፈሳዊ ውጊያ አስፈላጊነት አለ—ሥጋዊ የጦር ዕቃዎችን አለመጠቀም፣
የዕርገትን ስፍራ መጠበቅ፣
የጠላትን ምሽግ ለመስበር በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ የሆኑትን
መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን መጠቀም
እና ጸሎት ውጊያ እንደሆነ መረዳትና በሰማያዊው ክልል ያሉ
እና ከእግዚአብሔር ዙፋን የሚወጡ የውጊያ ጸሎቶችን መጸለይ።

© 2022 Living Stream Ministry

መልእክት አንድ

## ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መከናወን
## በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘካ. 1፡18-21፤ 21፡2፣ 5፣ 8-9፣ 11፤ 6፡12-13፤
10፡1፣ 3፣ 8፣ 12፤ 11፡7፤ 12፡1፣ 10፤ 14፡5፣ 9

**I. በብሉይ ኪዳን ያሉት የአሥራ ሁለቱ የታሪክ መጻሕፍት (ኢያሱ፣ መሣፍንት፣ ሩት፣ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል፣ 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት፣ 1ኛ እና 2ኛ ዜና፣ ዕዝራ፣ ነህምያ እና አስቴር) ውስጠ መሠረታዊ ትርጉም በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ለከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ መገለጡ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለማጠናቀቅ ቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ለማፍራት እና ለመገንባት ሰው በሕይወት እና በባሕርይ (ተመላኪነቱን ሳይጨምር) እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሰው በመሆን ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለማከናወን መንገድን የማዘጋጀቱ መገለጥ ነው፡-**

ሀ. አሥራ ሁለቱን የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ጋር ማያያዝ አለብን፤ መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ የሚነግረን አንድን ነገር ብቻ ነው—በእግዚአብሔር በጎ ደስታ፣ በልቡ መሻት ላይ የተመሠረተውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ (ኤፌ. 1፡4-5፣ 9-10፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 6፡3)፤ እነዚህ አሥራ ሁለት የታሪክ መጻሕፍት በእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ የተጻፉት ተግሣጽ እና አብርሆት እንድንቀበል ነው (1 ቆሮ. 10፡11)።

ለ. የዛሬውን የዓለም ሁኔታ ችግሮች ለመፍታት ብቸኛው መንገድ እርሱን መልሶ ለማምጣት ሙሽራው እንድንሆን እኛን ለማዘጋጀት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ (ከፍትሃዊ ቤዛነቱ የከንውን ሂደት እና ከሕይወታዊ ማዳኑ ግብ የከንውን ሂደት ጋር) መከናወኑ ነው; የእግዚአብሔር የልብ መሻት ይህ ነው፣ እርሱም ይፈጽመዋል—ሮሜ 5፡10፣ 17፣ 21፤ 1 ተሰ. 5፡23-24፤ ፊልጵ. 1፡3-6።

ሐ. የጌታ ዳግም መምጣት እንደ ኢ-ፍትሃዊነት (ኢሳ. 11፡4)፣ ጦርነት (2፡4)፣ ሕመም (ራእ. 22፡2፤ ሕዝ. 47፡12)፣ ራብ (ኢሳ. 35፡1፣ 6)፣ ትምህርት (2፡2-5፤ 4፡2-6፤ 11፡9፤ ዕንባ. 2፡14፤ ዕብ. 8፡11፤ መዝ. 2፡6፣ 12)፣ ኃጢአት የተሞሉ ተቋማት (ማቴ. 13፡41-43)፣ የፍጥረት ሁሉ መከራ (ሮሜ 8፡21-22፤ ኢሳ. 11፡6፣ 9) እና ምድራዊ መንግሥታት (ራእ. 11፡15፤ ዳን. 2፡34-35፣ 44-45) ያሉ የዓለምን ችግሮች ሁሉ ይፈታል።

**II. በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ወሳኝ ነጥብ እና ዋና ይዘት ለኢየሱስ ምስክር፣ ለእግዚአብሔር ግንባታ ሁለቱ የክርስቶስ መምጣቶች እንደሆኑ የዘካርያስ መጽሐፍ ይገልጣል፡-**

ሀ. ዘካርያስ ከ9 እስከ 11 ትሁት እና የቀርብ ስለ ነበረው ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያው ዝቅ ያለ አመጣጥ ይናገራል፡-

1. ክርስቶስ በጽድቅ መንገድ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ማዳን ይዞ እንደ ንጉሥ፣ ነገር ግን ዝቅ እንዳለ ንጉሥ፣ እንደ ተዋረደ ንጉሥ፣ በክብር ፈረስ ላይ ሳይሆን በአህያ ላይ፣ እንዲያውም በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ መጣ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ይህ ተፈጸመ—ዘካ. 9፡9፤ ማቴ.21፡5-10።
2. ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ በአንዱ ተጠላ፣ ተጠቃ፣ ተገፋ በሠላሳ ብር፣ በባሪያ ዋጋም ተካደ (ዘካ. 11፡8፣ 12-13፤ ዘጸ. 21፡32)፤ እዚህ በትንቢት የተነገረው በወንጌላት ተፈጽሟል (ማቴ. 26፡14-15፤ 27፡3-10)።
3. ክርስቶስ፣ የያሕዌ ባልንጀራ፣ ወደ እስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር-እንደተላከ እረኛ መጣ፤ እንደ ሰው ክርስቶስ የእስራኤል ልጆች ዘመድ እና የያሕዌ ባልንጀራ ነበር፤ እንደ እረኛ ተመቷል፣ ደቀ መዛሙርቱም እንደ በጎች ተበትነዋል—ዘካ. 13፡6-7፤ ዮሐ. 10፡11፤ ማቴ. 9፡36፤ 26፡31፤ ዮሐ. 16፡32-33።
4. ክርስቶስ በእስራኤል ቤት ውስጥ በመስቀል ላይ ቆሰለ፣ እርሱ ግን "በወዳጆቼ ቤት የቈሰልሁት ቍስል ነው" አለ፤ የእስራኤል ልጆች ክርስቶስን ገደሉት፣ ነገር ግን በዚህ ጣፋጭ ቃል ክርስቶስ ድርጊታቸውን ከወዳጆቹ እንደተቀበለው ቁስሎች ይቆጥረዋል—ዘካ. 13፡6-7፤ 12፡10፤ ራእ. 1፡7፤ መዝ. 22፡16።
5. የክርስቶስ ጎን ተወጋ፣ እርሱም ኃጢአትን እና ርኵሰትን [ለማንጻት] የተከፈተ ምንጭ ሆነ—ዘካ. 12፡10፤ 13፡1፤ ዮሐ. 19፡34፣ 37፤ ማቴ. 26፡28።

ለ. ዘካርያስ ከ12 እስከ 14 በኃይል እና በሥልጣን ስለሚሆነው ስለ ክርስቶስ አሸናፊ ዳግም መምጣት ይናገራል፡-

1. ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ በቅዱሳኑ፣ በድል ነሺዎቹ ታጅቦ ይመጣል—14፡5፤ ኢዮኤል 3፡11፤ ይሁ. 14።
2. እግሮቹ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ባለው በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ—ዘካ. 14፡4፤ ሐዋ. 1፡9-12።
3. ከሚከቧቸው አሕዛብ ለእስራኤል ልጆች፣ ለተመረጡት ሕዝቡ ይዋጋል፣ ከጥፋትም ያድናቸዋል—ዘካ. 14፡2-3፣ 12-15፤ 12፡1-9።

4. በዚያን ጊዜ የእስራኤል ቤት ሁሉ ወደ እርሱ ወደ ወጉት ይመለከታሉ፣ ለእርሱም ያለቅሱለታል፤ ከዚያም የተነሣ፣ እስራኤል ሁሉ ይድናል—ቁ. 10-14፤ ሮሜ 11:26።
5. ከዚያ በኋላ፣ በአሕዛብ ላይ ለመንገሥ እና ለመግዛት ንጉሥ ይሆናል፤ ሕዝቡ ሁሉ እርሱን ለማምለክ በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣሉ፣ ሁሉም ለእርሱ ይቀደሳሉ—ዘካ. 9:10፤ 14:16-21።
6. "እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል፤ በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ፥ ስሙም አንድ ይሆናል"—ቁ. 9፤ መዝ. 72:8፤ ራእ. 11:15።

**III. ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ለእግዚአብሔር መገለጥ የእግዚአብሔርን ግንባታ ለማግኘት በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ታሪክ ነው—ዘካ. 4:9፤ 6:12-15፤ ማቴ. 16:18፤ ዮሐ. 1:1፣ 14፤ 1 ቆሮ. 15:45፤ ራእ. 4:5፤ 5:6፤ 21:2:-**

ሀ. ክርስቶስ በሰው ታሪክ ውስጥ ያለውን የዓለምን ሁኔታ በሉዓላዊነቱ ለመቆጣጠር በጥበብ እየሠራ ሳለ፣ የእግዚአብሔርን የማይገደብ ጥበብ እና መለኮታዊ ንድፍ የሚገልጡ የሥራው ድንቅ የጥበብ ሥራ፣ የእግዚአብሔር ግጥም፣ የእግዚአብሔር አዲስ ፈጠራ ሊያደርገን በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ ጥበበኛ በሆነ መንገድ ራሱን ወደ ውስጣችን እየሠራ ነው—ሐዋ. 5:31፤ ኤፌ. 2:10።

ለ. ክርስቶስ በስብዕናው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በሸለቆው ታችኛው ክፍል በመዋረዳቸው ሊንከባከባቸው፣ ሊማልድላቸው እና ከባቢሎናውያን ምርኮ ፈጥኖ ሊያወጣቸው የቆመ የያሕዌ መልአክ፣ ያሕዌ ራሱ እንደ ሦስታንዱ አምላክ ነው—ዘካ. 1:7-17፤ ዘጸ. 3:2፣ 4-6፣ 13-15፤ ኢሳ. 63:9፤ ዘዳ. 33:27።

ሐ. አራቱን ቀንዶች ለመስበር እግዚአብሔር የተጠቀመበት የመጨረሻው የእጅ ሙያተኛ ክርስቶስ ነው፤ አራቱ ቀንዶች አራቱ መንግሥታት ከነገሥታታቸው—ባቢሎን፣ ሜዶ ፐርሺያ፣ ግሪክ እና የሮም ግዛት—በተጨማሪም በዳንኤል 2:31-33 አራት ክፍሎች ባሉት በታላቁ የሰው ምስል፣ በኢዮኤል 1:4 በአራቱ የአንበጣ ደረጃዎች እና በዳንኤል 7:3-8 በእግዚአብሔር የተመረጠውን ሕዝብ በጎዱት እና ባጠፉት በአራቱ አራዊት የተመለከቱ ናቸው—ዘካ. 1:18-21:-

1. አራቱ የእጅ ሙያተኞች እግዚአብሔር እነዚህን መንግሥታት ከነገሥታታቸው ለማጥፋት የተጠቀመባቸው ጥበባት ናቸው፤ የመጀመሪያዎቹ ሦስት መንግሥታት እያንዳንዱ (ባቢሎን፣ ሜዶ ፐርሺያ እና ግሪክ) ቀጥሎ ተከትሎት በሚመጣው መንግሥት ጥበብ በተሞላበት መንገድ ተያዘ—ዳን. 5፤ 8:3-7።
2. አራተኛው የእጅ ሙያተኛ፣ የተመለሰውን የሮም ግዛት የሚፈጨው በዚያም ተመልሶ በመምጣቱ የሰው መንግሥት ጥቅል-ድምር የሆነውን ታላቁን የሰው ምስል የሚፈጨው፣ እጅ ሳይነካው እንደሚፈነቀለው ድንጋይ ክርስቶስ ይሆናል—2:31-35።
3. ይህ ድንጋይ ክርስቶስን ብቻውን ሳይሆን ብዙዎች የተካተቱበትን ክርስቶስ፣ ክርስቶስን ከ"ኃያላኖቹ" ጋር ያመለክታል—ኢዮኤል 3:11።

መ. ብዙዎች የተካተቱበት ክርስቶስ፣ ክርስቶስ ከድል ነሺዋ ሙሽራው ጋር፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማምጣት የሰውን መንግሥት ጥቅል-ድምር ለመፍጨት እንደ ድንጋይ ይመጣል—ዳን. 2:34-35፤ ኢዮኤል 3:11፤ ራእ. 19:11-21፤ ተዛ. ዘፍ. 1:26።

ሠ. ዳንኤል 2 እጅ ሳይነካው እንደሚፈነቀለው ድንጋይ ስለ ክርስቶስ መምጣት ሲናገር፣ ራእይ 19 ሙሽራይቱ እንደ ሠራዊቱ እንዳለችው ማንነት ስለ ክርስቶስ መምጣት ይናገራል።

**IV. ኤፌሶን 5 እና 6 ቤተ ክርስቲያን ሙሽራም ተዋጊም እንደሆነች ይገልጣሉ፤ በራእይ 19ም ጭምር እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ገጽታዎች አሉን—ኤፌ. 5:25-27፤ 6:10-20፤ ራእ. 19:7-9፣ 11፣ 14:-**

ሀ. በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ፣ በሰው ታሪክ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ ሙሽራይቱ ለመሆን የሚያስውበው የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል፣ በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ፣ በሰው ታሪክ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ ተዋጊዋ ለመሆን የሚገድለው የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል—ኤፌ. 5:26፤ 6:17-18፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 3:16።

ለ. በሰርጉ ቀን ክርስቶስ ለዓመታት ከእግዚአብሔር ጠላት ጋር ስትዋጋ የነበረችውን ሙሽራውን፣ ድል ነሺዎቹን ያገባል—ተዛ. ዳን. 7:25፤ 6:10፤ ኤፌ. 6:12።

ሐ. የክርስቶስ ተቃዋሚውን እና የሰውን መንግሥት ጥቅል-ድምር ለማስወገድ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመውረዱ በፊት፣ ድል ነሺዎቹን ከራሱ ጋር እንደ አንድ አካል የሚያጣምርበት ሰርግ ይኖረዋል—ራእ. 19:7-9።

መ. ከዚህም የተነሣ፣ ክርስቶስ እንደ መንፈስ፣ በሂደት እንዳለፈው እና እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ፣ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሙሽራው፣ በሂደት እንዳለፈው እና እንደተለወጠው ሦስት ክፍል ያለው ሰው ያገባታል—22:17።

ሠ. ከሰርጉ በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ከነሠራዊቱ የሚዋጋውን የክርስቶስ ተቃዋሚውን ለማጥፋት አዲስ ካገባት ሙሽራው ጋር ይመጣል—19፡11፣ 14፡-

1. ጌታ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚውን፣ የዓመጽን ሰው፣ በአፉ እስትንፋስ ይገድለዋል፣ በመምጣቱ መገለጥም የክርስቶስ ተቃዋሚውን ያጠፋዋል—ቁ. 11-15፤ 2 ተሰ. 2፡2-8።
2. አሕዛብን ይመታበት ዘንድ ከክርስቶስ አፍ ስለታም ሰይፍ ይወጣል—ራእ. 19፡15፤ 1፡16፤ 2፡12፣ 16።

ረ. የሰውን መንግሥት ከፈጨ በኋላ፣ እግዚአብሔር መላውን አጽናፍ ዓለም ያጸዳል፤ ከዚያም ብዙዎች የተካተቱበት ክርስቶስ፣ ክርስቶስ ከድል ነሺዎቹ ጋር፣ ምድርን በሙሉ ለመሙላት ታላቅ ተራራ ይሆናል፣ ምድርን በሙሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ያደርጋል—ዳን. 2፡35፣ 44፣ 7፡22፣ 27፤ ራእ. 11፡15።

**V. ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መከናወን በሰው ታሪክ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን እንቅስቃሴ ለመፈጸም መንገዱ ክርስቶስን ሰባት እጥፍ እንዳየለው መንፈስ ለመለማመድ እና ለመደሰት መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ነው—1፡10፤ 4፡2፤ 17፡3፤ 21፡10፤ 4፡5፤ 5፡6፤ ዘካ. 3፡9፤ 4፡10፡-**

ሀ. ዘካርያስ 12፡1 "ስለ እስራኤል የተነገረ የእግዚአብሔር ቃል ሸክም ይህ ነው። ሰማያትን የዘረጋ፥ ምድርንም የመሠረተ፥ የሰውንም መንፈስ በውስጡ የሠራ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ይላል፡-

1. እግዚአብሔር በመፍጠሩ ውስጥ ሦስት ወሳኝ፣ እኩል በሆነ መልኩ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሠርቷል—ሰማያትን፣ ምድርን እና የሰውን መንፈስ።
2. ሰማያት ለምድር ናቸው፣ ምድር ለሰው ናት፣ ሰው እግዚአብሔርን እንዲነካ፣ እግዚአብሔርን እንዲቀበል፣ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ፣ እግዚአብሔርን እንዲኖር፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለእግዚአብሔር እንዲፈጽም እና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንዲሆን ከመንፈስ ጋር በእግዚአብሔር ተፈጥሯል—ቁ. 1።
3. የሰው ማንነት ማዕከላዊ መንግሥት እና ዋነኛው ክፍል መንፈሱ መሆን አለበት፤ በመንፈሱ የሚገዛ እና በዚያ ቁጥጥር ሥር ያለ ሰው መንፈሳዊ ሰው ነው—1 ቆሮ. 2፡14-15፤ 3፡1፤ 14፡32፤ ዮሐ. 3፡6፤ ኤፌ. 3፡16፤ 1 ጴጥ. 3፡4፤ ዳን. 6፡3፣ 10።
4. በዘካርያስ መጽሐፍ የተገለጠውን ክርስቶስ እንድንቀበል እና እርሱን በተመለከተ በዚያ የተገለጠውን ሁሉ እንድንረዳ ለመንፈሳችን ሙሉ ትኩረት እንድንሰጥ ዘካርያስ ያዘናል—ዘፍ. 2፡7፤ ዮሐ. 4፡24፤ ፊልጵ. 4፡23።

ለ. ክርስቶስን ሰባት እጥፍ እንዳየለው መንፈስ በሚከተሉት ገጽታዎች መደሰት ያስፈልገናል፡-

1. ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመፈተን፣ ለመፍረድ፣ ለመመርመር እና ለመንግሥቱ ለመውረስ በእጁ የመለኪያ ገመድ ያለው ሰው ነው—ዘካ. 2፡1-2፤ ሕዝ. 40፡3፤ 47፡1-5፤ መዝ. 139፡23-24።
2. "እኔ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ፥ በውስጥዋም ክብርን እሆናለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር"—ዘካ. 2፡5፡-
   ሀ. የኢየሩሳሌም ከተማ ቅጥር እና በውስጥዋ ያለው ክብር ያሕዌ ራሱ መሆኑ ያሕዌ እንደ ክርስቶስ በዙሪያዋ የኢየሩሳሌም ጥበቃ እና በማዕከሏም ክብሯ እንደሚሆን ያመለክታል፤ ይህ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የክርስቶስን ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት ያሳያል።
   ለ. ዛሬ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ማዕከል ያለ ክብር ነው፣ በተጨማሪም ለጥበቃዋ በቤተ ክርስቲያን ዳርቻ ዙሪያ የሚነድ እሳትም ነው፤ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሦስታንዱ አምላክ በክርስቶስ በማዕከሏ ያለ ክብር ይሆናል (ራእ. 21፡23፤ 22፡1፣ 5)፣ ይህም ክብር የከተማይቱ የእሳት ጥበቃ ለመሆን በብርሃን አሳላፊ ቅጥሯ በኩል ያበራል (21፡11፣ 18፣ 24)።
3. ክርስቶስ ለእርሱ በጣም ውድ ለሆኑት ለሕዝቡ እንክብካቤ በሠራዊት ጌታ የተላከው፣ በተጨማሪም ላኪው፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ጭምር ነው፤ እነርሱን የሚነካ ማንም የዓይኑን ብሌን ይነካል—ዘካ. 2፡8-9፣ 11፤ ተዛ. ዮሐ. 14፡26፤ 15፡26።
4. ክርስቶስ በጎቹን በሁለት በትሮች በእረኝነት በመንከባከብ እንደ እረኛ መጣ—አንዱ ሞገስ (ጸጋ) ተብሎ ሲጠራ ሌላኛው ማሰሪያ (ማሰር) ተብሎ ይጠራል፤ ጸጋ ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋሐዳችን ነው፣ ማሰር ደግሞ ወደ አንድነት ውስጥ ለመታሰራችን ነው—ዘካ. 11፡7፤ 2፡1-2፣ 5፣ 8-9፣ 11፤ ዮሐ. 21፡15-17፡-
   ሀ. ጌታ ለእኛ ብዙ ሞገስ ሲሰጠን ሳለ፣ የበለጠ ሞገስ፣ የበለጠ ጸጋ፣ የበለጠ "ዝናብ" እንዲልክልን ልንጠይቀው ይገባል—ዘካ. 10፡1፤ 12፡10፤ ሕዝ. 34፡26።
   ለ. በጌታ እንደ እረኛው ከተጎበኙ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለ እያንዳንዱ ደካማ በግ የክብር ፈረስ ይሆናል—ዘካ. 10፡3፤ ተዛ. 9፡13፣ 16፤ ዳን. 11፡32።

ሐ. አብዛኛውን ጊዜ በማለዳ መነቃቂያችን ጊዜ፣ ጌታ በፉጨት እየጠራን ወደ እርሱ ይሰበስበናል፤ የጌታ ፉጨት ጮክ ያለ ሳይሆን በትንሹ እንደ ወፍ ዝማሬ ያለ ለስላሳ እና የተረጋጋ ነው—ዘካ. 10፡8።

መ. ጌታ በስሙ እንድንመላለስ በራሱ ያጠነክረናል—ቁ. 12፤ ቆላ. 3፡17።

**VI. እንደ መለኮታዊው ታሪክ በሰው ታሪክ ውስጥ ባለው በእግዚአብሔር እንቅስቃሴ፣ አዲሱ ፍጥረት—አዲሱ ሰው ከአዲስ ልብ፣ ከአዲስ መንፈስ፣ ከአዲስ ሕይወት፣ ከአዲስ ባሕርይ፣ ከአዲስ ታሪክ እና ከአዲስ መጠናቀቅ ጋር—አለ፤ ጌታን መልሶ ለማምጣት ድል ነሺ ሙሽራው ለመሆን ራሳችንን እናዘጋጅ ዘንድ ለሕይወታዊ መዳናችን ምሥጢራዊ፣ መለኮታዊ ነገሮችን እየተለማመድን እና እየተደሰትን በመለኮታዊው ታሪክ ውስጥ ስላለን ጌታን እናወድሰዋለን—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #16፤ ሮሜ 5፡10፣ 17-18፣ 21፤ 6፡4፤ ሕዝ. 36፡26፤ 2 ቆሮ. 3፡16-18፤ ማቴ. 5፡8፤ ቲቶ 3፡5፤ ኤፌ. 5፡26-27፤ 6፡17-18፤ ራእ. 19፡7፤ ማቴ. 24፡44፤ 25፡10።**

*© 2022 Living Stream Ministry*